በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ዋልድባን ለመታደግ የሚንቀሳቀስ
ዓለም አቀፍ ጊዜያዊ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ

**Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**
**Save Waldba Monastery International Coalition**
**Washington, DC**

ለአቶ መለስ ዜናዊ
ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ሚኒስቴር
**<u>አዲስ አበባ</u>**

ጉዳዩ ፡- <u>ታሪካዊ የዋልድባ ገዳማችን ይዞታና የመነኮሳት ሰብዓዊ መብት እንዲከበርልን ስለመጠየቅ</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ታሪክ ማኅበራዊና ሥነ- ጥበብ እድገት ያበረከተችው አስተዋጽዖ ከኢትዮጵያ አልፎ በመላው ዓለም የሚታወቅ አውነታ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን ባላት ታሪክና መንፈሳዊ ሀብት ለበርካታ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ትልቁን ድርሻ የምትይዝ ሲሆን በዚህም መንግሥትንና የተለያዩ ተቋማትን ተጠቃሚ እያደረገች ስትገኝ ፤ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ቱሪስቶችም በዋነኛነት የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊያን ገዳማት አድባራት እና እንደ ጥምቀት መስቀል/ደመራ/ እና ልደት የመሳሰሉ ታላላቅ በዓላት መንፈሳዊ አከባበርን ለመመልከት እንደሚመጡ ዘወትር የሚመሰክሩት ነው ። በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ጥበብ እድገት ያበረከተችውን አስተዋጽዖ በየትኛውም ዘመን የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ይዘነጋዋል ብለን አንጠብቅም። በተለይም አሁን አገሪቱን እያስተዳደረ ያለው መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ኮሚሽንን የበለጠ አጠናክሬ እሰራለሁ ብሎ በተነሳበት ፤ በዚህ ሰዓት የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሆነባትን ቤተ ክርስቲያን ገዳማቷ እና አድባራቷ እንዲጠበቁ ማድረግ መንግሥታዊ የአስተዳደር ኃላፊነቱ ነው ።
ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ጥቃት በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም ሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ መድረሱ ፤ በወቅቱም መፍትሔ ሳይገኝላቸው እየተባባሱ መምጣታቸው የእምነቱን ተከታዮች የበለጠ እያሳሰበን መጥቷል። በእነዚህ ገዳማት እና አድባራት ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት እንዳይከሰት ማድረግ ፤ ጥፋቱን ያከናወኑ ሰዎችም በወቅቱ ፍርድ እንዲያገኙ አለመደረጉ ፤ መንግሥትም የቤተ ክርስቲያንን ይዞታ እና መብት በመጠበቅ ለሌሎች ጭምር ምሳሌ መሆን ሲገባው አገርን ለማስተዳደር ከወሰደው ኃላፊነት አንጻር የተከሰቱትን ችግሮች ስንመለከት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መንግሥትን ተጠያቂ እንደሚያደርገው አምነንበታል ። አንድን መንግሥት ትክክለኛ መንግሥት የሚያሰኘው ከሚያስተዳድራቸው ሕዝቦችና የሃይማኖት ተቋማት የሚቀርቡትን አቤቱታ ሰምቶ በወቅቱ ትክክለኛ ፍርድ እና አስተዳደራዊ ውሳኔ በመስጠት እንጂ የሚመራው ሕዝብና የሃይማኖት ተቋማት እንዲሰቀቁ የሚያደርግ ምላሽና እርምጃ በመውሰድ አይደለም ። የሕዝብን ድምጽ አለመስማት ፤ የቤተ ክርስቲያንንም አቤቱታ አለመቀበል ትዕግሥትን የሚፈታተን ፤ መፍትሔ ካልተሰጠውም ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ነገሮች እንዲሔዱ የሚያደርግ፡ አገርን የሚጎዳ፡ ታሪክንም የሚያበላሽ ክስተትን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። እኛም ይህንን ደብዳቤ የምንጽፈው መንግሥት አገርን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመገንዘብና በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት በአስቸኳይ እንዲቆም ለመጠየቅና የተሰማንን ሐዘን በምሬት ለመግለጽ ነው ።

ይህ ችግር ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በሰሜን አሜሪካ እና በተለያዩ ዓለማት የምንገኝ  የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች በየሳምንቱ በስልክ እንዲሁም በአካል በመገናኘት ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ በመነጋገር ላይ እንገኛለን። ይህንን ጉዳይ ለማሳሰብ

በአሜሪካና ካናዳ የተለያዩ ግዛቶች በርካታ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በተገኙበት በኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ዓለማቀፋዊ ተቋማት ቢሮዎች ሰላማዊ ሰልፍ አድርገናል። አሁንም ጉዳዮን  ለኢትዮጵያ መንግሥትና  ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ለማሳሰብና የዋልድባ ገዳም የቦታ ይዞታ  እና የመነኮሳትም ሰብዓዊ መብት እንዲከበር ግንቦት 27 ቀን 2004 ዓ. ም በአሜሪካና በካናዳ የተለያዩ ከተሞች ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ተላልፏል ።
ዋልድባ ገዳም መነኮሳት እያቀረቡ ያለውን አቤቱታ  ትኩረት ሳይሰጠው የተከበረው የቅድስና ቦታ ለልማት በሚል ሰበብ መንፈሳዊ ስሜትን በሚጎዳና ለቤተ ክርስቲያን  እየተሰጠ ያለውን ንቀት በሚያመላክት ደረጃ በመንግሥት ጭምር አሳዛኝ ምላሽ መሰጠቱ  ከፍተኛ ቁጣ  ፈጥሮብናል ። ስለዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት ስናቀርብ ለጥያቄዎያችን ዘላቂ መፍትሔ እንደሚሰጠን ተስፋ በማድረግ ነው ፦

1. የዋልድባ ገዳም የኢትዮጵያውያን ሁሉ መንፈሳዊ ሀብትና የተቀደሰ ቦታ በመሆኑ የገዳሙ መነኮሳት ባቀረቡት አቤቲታ መሰረት  የገዳሙ ክልል በማንኛውም ወገን እንዳይደፈርና ለልማታዊ ተግባር በሚል ሰበብ  የተጀመረው እንቅስቃሴ እንዲቆምልን ፤
2. የኢትዮጵያ ገዳማት እና አድባራት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ መንፈሳዊ ሀብትና የቅድስና ቦታዎች ስለሆኑ የቦታ ይዞታቸው በማንም እንዳይደፈር ማረጋገጫ  በመንግሥት  እንዲሰጥ፤
3. በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት እና ክርስቲያኖች  ላይ የሚደርሰው ጉዳት በግልጽ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን እንዲዘገብ ፤
4. የቤተ ክርስቲያንን መልካም ስም በሚያጎድፍ መልኩ ጥላቻቸውን የሚያንጸባርቁ የመንግሥት ባለሥልጣናት ከዚህ ተግባራቸው ተቆጥበው  ሕዝቡን  በትክክለኛ አስተዳደር እንዲመሩ  እንዲደረግልን ፤
5. የቤተ ክርሰቲያንን መብት ለማስጠበቅ የሚንቀሳቀሱ አባቶች እና ክርስቲያኖቸ ላይ ዛቻና አንግልት እንዲቆም እንጠይቃለን ።
6. በመንሥት ባለስልጣናት ገዳማውያኑ ላይ የተለየ የፖለቲካ ተልዕኮ ያላችሁ ናችሁ በሚል ሰበበ የሚደርስባቸው እንግልት በአስቸኳይ እንዲቆም።
7. በአሁን ሰዓት በገዳሙ ዙሪያ የምደርሰውን ዝርፊያና ምስበራ መንግስት ለገዳማውያኑም ሆነ ለቅርሶቹ አስፈላጊውን ክብካቤ እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

እግዚአብሔር አገራችንን  እና ገዳማችንን ይጠብቅልን

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ዋልድባን ለመታደግ የሚንቀሳቀስ
ዓለም አቀፍ ጊዜያዊ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ

**Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**
**Save Waldba Monastery International Coalition**
**Washington, DC**

ግልባጭ

- ለአፊዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለአፊዲሪ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
- ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
- ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ኦታዋ
- ለኢትዮጵያ ኤምባሲ  ዋሽንግተን ዲሲ
- ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
- ለብፁዓን አባቶች በያሉበት

Email: savewaldba@gmail.com |www.savewaldba.blogspot.com